# የአንጃው ቆይታ በአትላንታ

መርሻ ሲፈጠር ሁለት ጊዜ አህአፓ ልደቱን አክብሮለታል። አንደኛውን በደስታ ሁለተኛውን ግን በሀዘንና በሀፍረት ነበር ያከበረለት። የትናንቱ መርሻ ዛሬ የለም። ጊዜውን መስሎ ማተቡን በጥሷል። ዕርሙን በልቶ ከሰውነት ወጥቷል።ይልቁንም የቁም ሞት ሙቶ ሙሾ የሚደረድሩለት የሰ 4848;ድ ካድሬዎችና የወያኔ ሰላዮች ሆነዋል። በ05/30/08 አትላንታ ላይ የታዘብሁት ይህን ነበር።ለትዝብቴ መነሾ የሆነኝንም ኦብዘርቬሽን ያንጃውን ስብሰባ እንደወረደ አቅርቤዋለሁ። ከዚህ በታች የምትመለከቱት ዘገባ የስብሰባው ቃል ጉባኤ ነው። ራሴ የያዝኩት።

በእለቱ ተናጋሪ የነበሩት ሶሰስት ሰዎች ነበሩ። እነርሱም ዶ/ር ሰኢድ፤ ዶ/ር ወርቁና መርሻ ነበሩ። እንደ ቅደም ተከተላቸው። የመጀመሪያው ተናጋሪ ዶ/ር ሰይድ ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካዊና አኮኖሚያዊ ተጨባጭ ሁኔታ ነበር። ዶ/ሩ ግን ጊዜ ፈጅተው የተናገሩት በወሎ ከተማዎች በቅዳሜና 4608;ሙስ ገበያ የጨውና የሽንኩርት ዋጋ ስንት እንደ ዋለ ነበር። ከቤተሰቦቸ አገኘሁት ያሉትን ዜና ያካፈሉን።

ሁለተኛው ተናጋሪ ዶ/ር ወርቁ ነበር። ዶ/ር ወርቁ ንግግሩን ሲጀምር እኔ የምናገረው የግሌን ነው። ቡድን ወክየ አይደለም።

የቡድን ወይም የድርጅት ፖሊሲም አይደለም። የግል አመለካከቴን ነው። ባጠፋም እኔኑ ውቀሱ ብሎ ነበር ወደ ውይይቱ የወሰደን። የንግግሩ ርእስም ወያኔ በስልጠን ለመቆየት የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች የሚል ነበር። ቀጠሎም ወያኔ ስልጣኑን ላለመነጠቅ ከተራ ንግድ ስራ እስከ ፋብሪካና ባንክ ሱቃሱቅ?.. ሃይልንና ግድያን ጨምሮ በመጠቀም ስልጣኑን እንደ ያዘ ለመቆየት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ፈጥሮ እርስ በርሰ በሃይማኖትና በዘር ወይም በጎሳ በማጋጨት ከፋፍሎ ህዝቡን እቅም አልባ አስቀርቶታል። ባንፃሩም ተቃዋሚዎች በመከፋፈል አመች ሁኔታ ፈጥረውለታል። ድርጅ 726;ች ከምርጫው በፊት የነበራቸውን አንድነት ይዘው ቢቆዩ ኖሮ ወያኔ አሁን ባለበት ስልጣን አይቆይም ነበር። በመርጫው ቅንጅት አሸንፎ ግን ወያኔ አቸንፌአለሁ በማለት ስልጠኑን ይዞ ለመቆየት ችሏል በማለት ነጥቦቹን ?ሀ፤ ለ፤ ሐ፤ መ? ብሎ ደርድሯል።

ሶስተኛው ተናጋሪ መርሻ ነበር። የመርሻ የንግግር ርእስ ዲሞክራሲና ፍትህ ነበር። ያንጃው መሪ ንግግሩን ሲጀምር ?የ ኢተዮጵያ ፖለቲከኞች ስለ ዴሞክራሲ ብዙ የሚፅፉ፤ ብዙ የሚናገሩ ግን በተግባር የሶስተኛው ዓለም ሰዎች ናቸው።አምባገነኖች።በኛ በዴሞክራሲያዊ ኢ.ህአፓ ይህ እ& #4757;ደማይሆን ቃል እገባላችሁአለሁ።ጭብጨባ። ከሰላሳ አምስት አመት በላይ የታገልኩበት ድርጅት አህአፓ አምባገነን፤ ያባላቱን መብት የማያከብር፤አባላቱን በእኩልነት የማይመለከት፤ ግልፅነትና ተጠያቂነት የማይታይበት፤ ድርጅት ነው።በኛ በዴሞክራሲያዊ ኢ.ህአፓ ያባላት መ ብት አስጠባቂ ኮሚቴ አስመርጠን ግልፅነትንና ተጠያቂነትንም ለማረጋገጥ የቁጥጥር ኮሚቴ ተመስርቶ በመንቀሳቀስ ላይ ነን።ጭብጨባ። የምናራምደው ፖለቲካ ጨዋነት የተሞላበት፤ከ ስድብ የነፃ እንደሚሆን ቃል እገባላችሁአለሁ።ጭብጨባ።ካሁን በሁዋላ በድርጅቶች ጣልቃ መግባ 5; አንዱን ከሌላው ማናከስና መከፋፈል በኛ በዲክራሲያዊ ኢ.ህአፓ ፈፅሞ አይከሰትም። ዴሞክራሲያዊ ኢ.ህአፓ፥__

* ያለውን መንግስት በጠላትነት ከፈረጁ

* በትዮጵያ ልእዋላዊነት ላይ ጥርት ያለ

አቋም ካላቸው

* በፍትህ በእኩልነትና ባንድነት ከሚያምኑ ሀይሎች ጋር ህብረት ፈጥሮ ለመስራት ዝግጁ ነው። ለዚህም ግብ ካንድአንድ ድርጅቶች ጋር ንግግር ጀምረናል።ስህተት የፈፀሙትንም ስህተታቸውን በማረም በህብረት መታገል ይቻላል። ዲሞክራሲን እያንዳንዱ ድርጅት ማቀፍ አለበት።ኢህአ 47; ውስጥ ያባላት መብት ባለመከበሩ ድርጅቱ ከሁለት ተከፍሏል። ግን በሁለቱም በኩል ያሉ አባላት በክፉ አይተያዩም። እንደ ሃውልት ለብዙ ጊዜ ስልጣን ይዘን ቆይተናል።በኛ ድርጅት ከሁለት ጉባኤ በላይ ባመራር መቀጠል አይቻልም። ኢህአፓ ሌሎችን በመክሰስ፣ሌሎችን በመተንኮስ፣መ 4612;ድ የለበትም። መዘላለፍ መዘራጠጥና መሳደብ የፖለቲካ ባህል አይደለም። ዲሞክራሲያዊ ኢህአፓ ይህንንም ያወግዛል።ሌሎች ድርጅቶች ውስጥ እየገቡ እነርሱን ማዳከም ይልቁንም በሰለጠነ መልክ በስርአት ልዩነቶችን ለመግለፅና ባርያነት ለመቀጠል እንፈልጋለን፡፣ለዚህ ተባበ ;ን ብሎ ጨረሰ።

1ኛ ጥያቀ አበበ?እንዳሉት ከሁለት ተከፍላችሁዋል?

ለሁለት ስትከፈሉ ብዙ ለድርጅቱ ፍቅር ያላቸውን ጓዶች ምን ይሰማቸዋል ብላች ነበር?

ስለ ህዝባችን ችግር በውይይት መፍታት ይቻላል ብለዋል፣ ግን እኛ ኢህአፓዎች ያልተስማማን እንዴት ብለን ነው ከሌሎች ጋር መወያየትና መግባባት የምንችለው?

2ኛ ጥያቄ መኳንንት ስለ ሀገራችን ችግር በሰፊው ተነግሮናል፣ዛሬ የሰማነው ኢህአፓ ከሁለት ተከፈለ ተብሎ ነው፣ የራሳችንን ችግር ለረዥም ጊዜ በትግል ያሳለፍነው ኢህአፓዎች ተራርመን ችግሩን ለመፍታት ያልቻልን ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ለመግባባት እንዴት እንችላለን?

ኢህአፓ ይህን ያክል ጊዜ ታግሎ ዛሬ ሲከፈል በድርጅቱ መሃል የነበረውን ቸግር ለመፍታት ምን ያክል ሞክረህ ነው ዛሬ ዴሞክራሲ የለም የምትለን? አንተ ስትኖርበት ዲሞክራሲ ይኖራል አንተ ጥለህ ስትወጣ ግን ድርጅቱ ውስጥ ዲሞክራሲ የለም ስትል ሰው ይታዘበኛል አትልም?

3ኛ ጥያቄ ወርቁ አቶ መርሻ የማከብርዎ ሰው ነዎት። የናንተ መከፋፈል ግን አሳፋሪም አሳዛኝም ነው።ልዩነት ልዩነት ስትሉ ልዩነት ለጠራትም ሊሆን ይችላል ግን እስከመቼ?

4ኛ ጥያቄ ዶ/ር ፍስሀ ማንኛውም ድርጅት ለተወሰነ ጊዜ ሄዶ ማደግ ካልቻለ መከፋፈሉ አግቦነት አለው። ስለዚህ አቶ መርሻ እንዳሉት ለመከፋፈል ሁኔታ ካለ መከፋፈሉ እድገት ነው የሚሆነውና ባቶ መርሻ ለይ ጫና እንዳይደረግ አደራ እላለሁ።

አሁን የማእራቡ ተወሰደ ቀጥሎ ወደ ደቡቡ ክፍል የሚቀጥል ይመስለኛል ይህን ሁኔታ በምን ኢመርጀንሲ ታዩት አላችሁ?

5ኛ ዓለሙ ያይኔ እኔ የምሰጠው አስተያየት ነው። አቶ መርሻን ሁለት ጊዜ ነው ያየሁዋቸው። ዛሬ ሳያቸው ግን ትልቅ ትልቅ ለውጥ አይቻለሁ። ይህ ድርጅት ትግሉን ለመምራት የሚያስችል ተመክሮ እያለው ግን ዝም ብሎ በመኖሩ የትም አልደረሰም።ድርጅቱ ያባላቱን መብት የማይጠብቅ ከሆነ 773;ንዴት ለሌላው ሰው መብት ሊሰጥ ይችላል።ስለዚህ አይደለም አንድ ጊዜ ዘጠኝ ጊዜ መሰነጣጠቅ ሲያንሰው ነው። ሌላው ግን ከዶ/ር ሰይድ ጠብቄው የነበረው ሌላ ነው እርሳቸው ግን የነገሩን የጤፍ ዋጋ

1000 ብር መሆኑን ነው።

መልስ

መርሻ ይህንን ነገር ወደ ዝርዝር ያልገባሁት በጠያቂ እንደሚመጣ ስላወቅሁ ነው። ለምን ኢህአፓ ከሁለት ተከፈለ? ኢህአፓን አለኝታየ ይለው ለነበረው ህዝብ መከፋፈሉ እንደሚያዳክመው እናውቃለን። ግን ሃያና ሰላሳ አመት ተሸክሞ ለምን በ30ኛው ዓመት ጥላችሁ ወጣችሁ ወጣችሁ ማለት 25;ክክል አይደለም።መከፋፈል አዲስ አይደለም፡፤ አዲስ አበባ ውስጥም አንጃ ተብሎ ወደ ደርግ ጠላትነው የሚባለው?ገብተው ጉዳት ድረሷል።አሲምባ ውስጥም እንዲሁ ችግር ተፈጥሮ መከላከል ተደርጓል። ቀጥሎም ብተና ተደርጎ ለስደትና ወደ ደርግ ሄደዋል። በነዚያ ጊዜዎች ድርጅትን ለ 4635;ዳን የውስጥ ችግርን ትኩረት ለመስጠት አይቻልም ነበር።በከተማ ቀይ ሽብር ነበር፡፤ በገጠርም ለመሰብሰብ የነበረው ከበባ ለውስጥ ልዩነት ጊዜ የሚሰጥ አልነበረም። በዚያ ጊዜ ችግር አልነበረም ማለት አይደለም።ዛሬ ግን ከዚያ በሁዋላ ያንጃ ቡድን አለ። ያባላት ጉደይ ሲነሳ አ 7;ጃ መሪዎች አጅና እግራችንን ጠፍረው ሊይዙን ችለዋል። በዚህም አኳያ አንጃው ከጠላት ጋር ውይይትና ግንኙነት አድርጓል። እኛ ሳናውቀው ሁለት ግለሰቦች ወደ ሻቢይ ሄደው ተገናኝተዋል። የጉባኤን ቦታ ቀይረዋል። ይህንን ችግር አላሰራ ያለንን ሁኔታ ነው እረግጠን የወጣነው።ዕመ 4653;ታ ነው። የስድብ ፖለቲካ ካሁን በሁዋላ በኢህአፓ ይኖርም። መታፈን በቃን አልን። ያንጃው አደራጆች በጉባኤው የመጡ አባላትን እኩል መብት አይኖራቸውም አሉ።ባንዳንዶቹ ላይ አሉባልታ ተነዛ። ኢህአፓ ተከፈለ። አሁንም እነርሱን እንደጠላት አናይም። በስህተት የተቀሰቀሱ ጥሩ ጓዶች ቀርተዋል። የተወሰኑ የቡድን አመራር ነበሩ እገሌ ሲአይኤ ነው እገሌ ወያኔ ነው ብለውናል።እኔ መርሻ በትግል ነው የምሞተው። በትግሌ የሚሳለቁ የቀድሞ አባላትን እንዳይሰባሰቡ የሚታገሉ ሰለሆኑ እነርሱን ይዘን መቀጠል አንችልም። ስለዚህ ዶ/ር ፍስሀ እንዳለው መከፋፈሉ 616;ህዝባችን ትግል አመርቂ ሁኔታን እንፈጠራለን። እንዱ ይጫጫል። በጉባኤው 75%ቱ ከኛ ጋር ነበር።ስለሆነም ይህን ቡድን ጥለን መውጣት ተገደናል። ወያኔ ናቸው ማለት አሉባልታ ነው።ያ ቡድን ኢ--ዲሞክራሲያዊ ነው።እኛም እየሰራን ያለነው ያን ቡድን ተፃረን ነው።

ተጨመሪ ዶ/ር ወርቁ---- በድርጅት ውስጥ ግለፅነት መኖር አለበት።አንድን ድርጅት ለመገንባት በግልፅ ውይይት መደርግ አለበት።

ተጨማሪ ዶ/ር ሰይድ--- በድርጅቱ ውስጥ ኮንግረስ ከመካፈል በስተቀር ብዙም አለውቅም።እኔ ደግሞ ተባበሩ ነበር ያልኩት።እንዳውም መከፋፈሉ ተልእኮ ነበረው።መሰዳደብ ይቅርታ የሚደረግለት አይደለም።ላስታርቅ ሄጄ ተባርሬ መጣሁ።

ጥያቄ

አስማማው ታዝቤ ከምሄድ ያየሁትን ልናገር፡፤ አቶ መርሻ እኔም በስብሰባው ነበርኩ። አሁን የምሰማው እናንተ ብዙሃን እንደነበራችሁ ነው። ውሸት ነው። አልነበራችሁም። ሌላው ወገን አጭበርብሯል ላልከው ያጭበረበራችሁ አናንተ ናችሁ።ከሁለቱም ወገን ስህተት ነበር።ግን እና 7;ተ ያመጣችሁት ብዛቱ ሆቴሉን አጥለቅልቆት ነበር።ያም ሆኖ ብዙሃን መሆን አልቻላችሁም።ስብሰባው ከተጀመረ በሁዋላም አባላት ሁለቱንም ወገን ገምግመው መፍትሄ ለመስጠት ተዘጋጅተው ሳለ አንተ ሌሊቱን በደበበ ሾፌርነት ጠፍተህ አደርክ።የቀራችሁትም ጧት ተነስታችሁ ስብሰባው ን እረግጣችሁ ወጣችሁ። ሌላው ግን

መቼ ነበር ኢ.ህአፓ አመራሩን ያልመረጠበት ጊዜ አቶ መርሻ? አንተ የተመረጥከው ሌሎች ሲጠቆሙ ቤተሰቤ እገሌ መሌ ስለሚሉ ነበር ደግመን ደጋግመን የመረጥናችሁ። ይህም የሆነው አናንተ በፕሮፌሽናል መስራት ሰለምትችሉ እንጂ አምባገንንነት በድር 869;ቱ ሰለሰፈነ አይደለም።እውን የምትናገረው እውነት ነው? ብሎ አዳራሹን ጥሎ ወጣ።

መልስ

መርሻ ወደ ዝርዝሩ አልገባም።ብዙ መዝረክረኮች ነበሩ፤በመጀመሪያ አህጉራዊ ኮሚቴው ማጣራጥ ነበረበት ግን ስራውን እንዳይሰራ በኮሚቴው ውስጥ አንጃው አለሰራ አለው። ቀጥሎ ማጣራቱን መስራት የነበረበት የሰሜን አሜሪካ ከአኮ ነበር በዚህም ኮሚቴ ያንጃው ቡድን ሁለት አባላ 725; አልሰበሰብም አሉ።ጉዳዩ ተንከባሎ ተንከባሎ ነው ወደ ጉባኤው የመጣው።ይህም ብቻ አይደለም ጉባኤ ለመወሰን አንጃው ችግር ፈጥሮ የጉባኤ ቦታና አዘጋጅም ባንጃው ችግር ፈጣሪነት የተፈለገው አልሆነም። ጉባም ከተገባ በሁዋላ ሊቀመንበር ሆኖ የተመረጠው ለህዋስ መሪነት የማይበ& #4675; ሰው ነበር። ይህን እያየን ከዚያ መቆየት ጊዜን ማባከን ነው። ከዚያ የቀራችሁት ድርጅቱን ቀብራችሁታል።

ቀጣዩ ተናጋሪ አብርሃም ነበር። ግን ደበበ ሊቀመንበሩን አሰፌን በጆሮው ቀሪውን ጊዜ አንተ ጨርሰው ስላለው ንግግር ሲጀምር ከቤቱ ጩኸት በረከተ።ስጠው ስጠው የሚል።የናንተን ጊዜ ጨርሳችሁዋል ቀሪው ጊዜ የኛ ነው ብዙ ጥየቄዎች አሉን አሉ። ተናጋሪው መሰረታዊ ጥያቄዎችን አንድ ሁለት እያለ ሲደረድር ያንጃው ተከታዮች ቀማው ቀማው ማለት ጀመሩ።ቀጥሎም መይኩን ከነሲቡ እጅ ደበበ ቀምቶ ወሰደውና በፓልቶክ ይተላለፍ የነበረው ተቋረጠ።ሆኖም ለነበረው ህዝብ ያንጃውን መሪ ማንነት ተናጋሪው አስረግጦ ውርደት አከናንቦ አሰናበተው።መርሻም አንገቱን አየ ;ቀነቀ ከንፈሩን እንደነከሰ ስብሰባው ተዘጋ።

መጠቃለያ

ወደ ስብሰባው ስገባ የቆጠርኩት የሰው ብዛት ሃያ ነበር።ተናጋዎቹን ጨምሮ ጠቅላላ ብዛቱ ሃያ ሶስት ነበር።ከዚህ ውስጥ ሶስቱ የወያኔ (ሰላይና ሁለት) ደጋፊዎች ነበሩ። ሶስቱ ደግሞ የብርሀኑ ነጋ ሰዎች ነበሩ። አምስቱ የኢ.ህአፓ፣ ስምንቱ ደግሞ ያንጃው አባላት ናቸው። ያንጃው የ 47;ልቶክ አቀናባሪ አቶ ነሲቡ ግን መቶ ሰው እያዳመጠ ነው ሲል አዳምጫለሁ። ነጭ ወሸት።

abraham beyenne